# " ሰቆቃ ወ ድንግል "

‹‹አይቴ ኀለፈት እምዕያማ ማርያም ጣዕዋ
ኀሤሥክዋ በቤተልሔም ወኢረከብክዋ
እሴእለክሙ ሰብአ ሰገል ገሊላ እመ ርኢክዋም
ንገሩኒ ዜናሃ ወአርእዩኒ ፍናዋ
ኀበ ሖረት በብካይ እትልዋ››

ትርጉም፡- የገሊላ ሰዎች ሆይ ማርያም እንቦሳ፤እንቦሳ ልጇን ይዛ ከማደሪያዋ ወዴት ሄደች? በቤተልሔም ፈለግኋት አላገኘኋትም እርሷን በልቅሶ እከተላት ዘንድ ዜናዋን ንገሩኝ መንገዷንም አሳዩኝ እያልኩ አለምናችኋለሁ።

ሐተታ፡-እመቤታችንን እና ጌታን እንቦሳ ማለቱ ስለምን ነው? ቢሉ እመቤታችን ከመፅነሷ በፊት ኢያቄምና ሐና በሕልም ነጭ እንቦሳ ከበረታቸው ስትገባ፣ስትወጣ እንቦሳይቱም እንቦሳ ስትወልድ አይተው ነበርና ድንግል ማርያምንንና ልጇን በእንቦሳ መሰላቸው።

‹‹ርኢክሙኑ ወለተ ደክታመ
ሐዚላ ሕጻና ትኅይይ ገዳመ
አኅሥሠኪ ወእብል እንዘ አዐይል አድያመ
ምርያም ጸዋሪት ኃይል ዘኢለመድኪ ድካመ
አንደደኒ ሥራሕኪ ከዊኖ አፍሐመ››

ትርጉም፡-ሕማምን ያልለመድሽ፣ኃይልን(ኢየሱስ ክርስቶስን)የተሸከምሽ ድንግል ማርያም መከራሽ እሳት ሆኖ አቃጠለኝ ልጇን አዝላ ወደ በረሃ ስትሸሽ ደሃ አደግ የሆነች ድንግል ማርያምን እይታችኋልን? እያልኩ፣አውራጃውንም እየዞርኩ እፈልግሻለሁ።

ሐተታ፡-እመቤታችንን ደሃ አደግ ማለቱ በትንሽነቷ ከወላጆቿ ተለይታ በቤተ መቅደስ ማደጓን ሲያሳይ ነው። ሕማምን ያልለመድሽ ማለቱ ደግሞ እመቤታችን ልዑለ ባሕርይ ኢየሱስ ክርስቶስን በማሕፀኗ ስትሸከም ድካም አላገኛትም ነበርና ማለትም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ስትወልድ፣ከወለደችም በኋላ የሴቶች ልማድ አላገኛትምና ከኀልዮ፣ከነቢብም ሆነ ከገቢር(ኃጢአትን ከማሰብ፤አስቦም ከመናገር፣ተናግሮም ከመፈጸም)ንጽሕት ናትና ሕማምን ያልለመድሽ አላት።

‹‹ርኢክሙኑ ነአሰ መርዐተ
ሐዚላ ሕፃና እንዘ ተሐውር ፍኖተ
አኅሥሠኪ ወእብል እስከ እትከደን መሬተ
ማርያም ፈላሲተ ቁስቋም ዘአልብኪ ቤተ
አውዐየኒ ንግደትኪ ከዊኖ እሳተ››

ትርጉም፡- ማደሪያን አጥተሽ ቁስቋም ወደሚባል አገር የተሰደድሽ ድንግል ማርያም ስደትሽ እሳት ሆኖ አቃጠለኝ ከመሬት ተፈጥሬአለሁና ወደ መሬትም እስከመለስ ድረስ ልጇን አዝላ መንገድን ስትሔድ ትንሽ ሙሽራን አይታችኋልን? እያልኩ እፈልግሻለሁ (ስደትሽን አስባለሁ)።

ሐተታ፡-እመቤታችንን ትንሽ ሙሽራ ማለቱ፡- እመቤታችን በቁመትና በስፋት እንደማንኛውም ሰው ስትሆን በክብር ግን ከመላእክትና ከፍጡራን ሁሉ ትበልጣለች አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው ‹‹እንዘ ንስቲት አባል አንቲ፣እንዘ ንእስት መርዓት አንቲ›› (በሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት የተወሰንሽ የ 15 ዓመት ቆንጆ(ልጃገረድ) ስትሆኚ ዙፋኑ እሳት የሆነ ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ በማሕፀንሽ ወሰንሽ) ሲል ተናግሯል ለዚህ ክብሯም አንክሮ(ዕፁብ እያሉ ማድነቅ) ይገባል እንዲል በቅዳሴ ማርያም ትርጉም ቁ 77-80።

‹‹እምሐልኩክን በኃይሉ ወበፅንዑ ለገዳም አዋልደ ኢየሩሳሌም
እመ ረከብክዋ ለማርያም በደብረ ቁስቋም
ከመ ታይድዓሃ ገብራ ሕርቱም
ዘሀሎኩ ጽዑርየ በዓለም ሕሙም››

ትርጉም፡-የኢየሩሳሌም ልጆች ሆይ መከራ በበዛበት በዚህ ዓለም ተቸግሬ ያለሁ የእኔን የአገልጋይዋን ልቅሶ እነግራት ዘንድ ቁስቋም ወደሚባል አገር ድንግል ማርያምን ካገኛችኋት(ያገኛችኋት እንደሆነ)ተአምር ማድረግ በሚችል አንድ ልጇ አማጽኛችኋለሁ፣እማጸናችኋለሁ።

‹‹አመ ዐረጉ በእግረ ኀሊናየ ውስተ ደብረ ቁስቋም ለይባቤ
ርኢኩ ድንግል በፍኖተ ዘሰለብዋ ግንባቤ
ሐዚላ ሕፃና ዘወለደት በኢሩካቤ
እምፃማ ድካም እንዘ ታስቆቁ ወትቤ
ንእስት አነ ዘኢለመድኩ ምንዳቤ
ወልብየ ተሐውከኒ ከመ እብኪ ሶቤ››

ትርጉም፡-ለምስጋና በሐሳብ እግሬ ወደ ቁስቋም ተራራ በወጣሁ ጊዜ ያለ ሩካቤ በድንግልና የወለደችውን ልጇን አዝላ ከፍጹም ድካም የተነሣ ‹‹እኔ መከራን ያልለመድኩ ትንሽ ነኝ›› እያለች ስታለቅስ በመንገድ ልብስን የቀሟትን ድንግል ማርያምን አየሁ ያን ጊዜም ልቤ ታወከ።

**“አይ...አይሆንላቸውም” ......ለምን ይለፋሉ?”ቢባሉ ምን ይሰመዎታል ይሆን?**

=====================================

ታልቅ ምኞት ካለህ አንድ ታሪክ ላስታውስህ ወንድሜ....

"በተራራ ታላቁ ሩጫ"

++================+++

ተራራው ትልቅ ነበርና ውድድሩን የሚመለከተው ሁሉ “አይ...አይሆንላቸውም”፤ “ተራራው ጫፍም በፍፁም አይደርሱም” “ኤሊ እኮ ናቸው እንዴት ሊሳካለቸው ይችላል”፤ “ሽረ አሁን ይወድቃሉ” “ሆ ሆ የማይሆን ነገር ...ለምን ይለፋሉ?” ይላል። ሁሉም የተሰማውን

ይሰነዝራል።አንድም ተመልካች አንዳቸውም ከተራራው ጫፍ ይደርሳሉ ብሎ ያመነ አልነበረም።የተመልካቹን ጩኸት ተከትሎ ፤ቀስ ቀስ እየለ....ተወዳዳሪዎቹ አንድ በአንድ መቀነስ ጀመሩ፤ አንድ በአንድ ተስፋ እየቆረጡ....ከውድድሩ ወጡ። ጥቂቶች በተስፋ ውድድሩን ይቀጥሉ ጀመር። ተመለካቹ “የማይሳካ ነገር ነው.....ቆይ አሁን ያቋርጡ የለ” ይላል። ውድድሩ በገፋ ቁጥር የተወዳዳሪዎቹም ቁጥር መቀነሱን ቀጠለ...... በመጨረሻ አንድ ኤሊ ብቻውን ቀረ። ያ ኤሊ ተራራውን መውጣቱን ተያያዘው.....ውድድሩን ያቋረጡትን ኤሊዎችን ሳይመለከት ብቻውን ገሰገሰ።

ተመልካቹ አሁንም እንደማይሳካ ቢጮህ እሱ ግን መንገዱን ከራሱ ጋር ተያያዘው። እንዳሰበውም ከተራራው ጫፍ ደረሰ። ይህ ሁሉንም ያስገረመ ነበር። ውድድሩን ያቋረጡት ኤሊዎች እና ተመልካቾች ይህ ኤሊ ብቻውን ውድድሩን እንዴት እንደጨረሰ

ገረማቸው.....ሊጠይቁት ሲሄዱ ግን፤ ያ ውድድሩን ያሸነፈው ኤሊ የማይሰማ ደንቆሮ ሆኖ ተገኘ። የአሸናፊነቱ ሚስጥርም የማንንም ጩኸት እና ንግግር ባለመስማቱ ነበረ።

==================================

ታልቅ ምኞት ካለህ፤ ጆሮህ ሌላውን አይስማ፤ “አይቻልም” “የማይሆን ነገር ነው” የሚል ተመልካች ሞልቷልና ዝም ብለህ መንገድህን ተጓዝ። የተመለካቹን ንግግር የምንሰማ ከሆነ.....የነፍሳችንን ጥሪ መስማት ያቅተናል፤ አላማቸንን በእንጭጩ ይቀጩታል፤ ልንኖርለት የሚገባንን ህልም ቅዠት

ያደርጉታል። “አይቻልም” “አይሆንም” ሲሉ.......ነገሩን በራሳቸው አቅም መዝነው መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ህልም ካለን፤ አላማ ካለን፤ የምንኖርለት ነገር ካለ፤ ጆሮዋችንን ደፍነን መጓዙ ይጠቅመናል።

የተመላካች አፍ የስንቱን ተወዳዳሪ ተስፋ አጨለመ፤ የስንቱን የተስፋ ጭላንጭል በትንፋሻቸው አጠፋ? የስንቱን ጉልበት አንበረከከ። ተራራውን በስኬት ወጥተው የምናያቸው ሰዎች ሁሉም፤ ውድድሩን መጀመሪያ ሲጅመሩ ብቻቸውን አልነበሩም፤

እጅግ ብዙ ሰው አብሮ ተሳትፏል። ነገር ግን አሸናፊ የሆኑት የሰውን ጩኸት ያልሰሙት ብቻ ናቸው። እኔም እናንተም ልንደርስበት የምንጓጓለት ትልቅ የህይወት ተራራ ይኖራል.......እናም ከጫፉ ለመድረስ ከፈለግን ጆሮዎቻችን አሉታዊ ነገሮች እንዳይሰሙ እንድፈናቸው።

**3 ዛፎች ነበሩ ። ይለናል ዋናው ባለታሪኩ...**

---

3 ዛፎች ነበሩ ። 2 ቱ የቆሙ ሲሆኑ አንዱ ግን ወድቋል። ከእለታት አንድ ቀን እኚህ ዛፎች የህይወት ህልማቸውን ይነጋገሩ ጀመር ።

አንደኛው ዛፍ " እኔ ሳጥን ሆኜ የአለም ውድ እቃዎች እንዲቀመጡብኝ ጥልቅ ምኞቴ ነው " አለ፣ ሁለተኛውም ቀበል አድርጎ " እኔ መርከብ ሆኜ የአለም ነገስታት እንዲጓጓዙብኝ እንዲፈንጩብኝ እፈልጋለው" አለ ፣ ሶስተኛው ደግሞ " እኔ መድሀኒት ሆኜ ብዙዎችን ማዳን ከቻልኩ ከዛ በላይ ምንም ኣልፈልግም" አለ ።

ሶስቱም ህልማቸውን አውርተው ሲጨርሱ ዛፍ ቆራጮች መጡ፡ የወደቀውን ይዘውት ሄዱ ። እሱም ሳጥን መሆን የህይወት ፍላጎቱ ቢሆንም ጠርበው የከብቶች መመገቢያ አድርገው ሰሩት። ሁለተኛውንም መጥተው ቆረጡት ለጀልባነትም አዋሉት፡ መርከብ የመሆን ምኞቱም ባክኖ ቀረ።

ሁለቱም ዛፎች ተናደዱ ህልማቸው የተጨናገፈም መሰላቸው። ሶስተኛው ዛፍም ለምንም አገልግሎት ባለመዋሉ እጅጉኑ አስከፋው።

ከአመታት በኋላ ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ አለም መጣ። እነሆ በ ቤተልሄም ቦታ ስላልነበር በከብቶች በረት ተወለደ። እናቱ ማርያምም በከብቶች መመገቢያ ውስጥ ጠቅልላ አስቀመጠችዉ። የአለም ውድ ነገሮች ማስቀመጫ መሆን የፈለገው ዛፍም የውዶች ውድ የእንቁዎች አንቁ የሆነው ክርስቶስ ተቀመጠበት።

ጌታም ሊያስተምር ሲሄድ በታንኳ ተጓዘ ፡ ያም ታንኳ ያ የአለም ነገስታት እንዲጓዝብኝ እፈልጋለው ያለው ነበር፡ የነገስታት ንጉስም ተጓጓዘበት።

ጌታችን እንዲሰቀል ሲፈረድበት የቀረውን ዛፍ ቆርጠው አመጡ በሱም ሰቀሉት። ለብዙዎች መድሀኒት መሆን

የፈለገው ዛፍ መስቀል ሆኖ አለም ሁሉ ዳነበት።
ሶስቱም ዛፎች ህልማቸው የተጨናገፈ ሲመስላቸው ፈጣሪ ግን ካሰቡት በላይ አደረገላቸው።በጥቂቱ የተመኘ በብዙ ይሰጠዋል ወዳጆቼ ለእኛም ከራሳችን በላይ የሚያስብልን ምርጥ አምላክ አለን። ስለዚህ ህልማችን የተጨናገፈ ቢመስለን አምላክ አብዝቶ ሊሰጠን ስለሆነ ሁሌም በ ትዕግስት እንጠብቀው።
መጪው አዲስ ዘመን ሁላችንም የተፈጠርንበትን አላማ አውቀን ፈጣሪ አምላካችንን የምናስደስትበት ብሩህ አመት እንዲሆን የልብ ምኞቴ ነው።የኢዮብን ትዕግስት አምላካችን ለሁላችንም ያድለን ።.

።። ሕግጋተ እግዚአብሔር ።።
።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።።
1. ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ):-
2. አሠርቱ ቃላት: /አሠርቱ ትዕዛዛት/ /አሠርቱ ሕግጋት/ /ሕገ መጽሐፍ (ሕገ ኦሪት)/:-
3. ስድስቱ ሕግጋት /ስድስቱ ትዕዛዘተ / /ስድስቱ ቃላተ/ ወንጌል:-
4. አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን:-
5. በለተ ምጽአት ከጌታችን የምንጠየቃቸውና የምንመልሳቸው 6 ጥያቄዎች:-
ከላይ በተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ሕግጋት ማብራሪያ ተሰቶባቸዋል አንብበው ይጠቀሙ:+

+እግዚአብሔር አማላክ ፈጣሪ እንደመሆኑ ፈቃዱ የማይለወጥ ቀዋሚ ስለሆነ ጊዜያዊና ቅጽበታዊ ፍጥረት አልፈጠረም: ፈጥሮም ያለዓላማ: ያለሕግ ያለሥርዓት አልተወም።
በዓለሙ ሙሉ የሆነ እግዚአብሔር ሕግጋቱም ሁሉን የሚመለከትና ለዓለሙ ሁሉ ቀዋሚ የሆኑ ሕግጋት ናቸው። እነዚህም:- ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ) : አሠርቱ ቃላት: ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው።
**።።1።። ሕገ ልቦና (የሕሊና ሕግ):-**
በሰው ልቦና አንድ ጊዜ ከተጻፈ ሳያረጅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የሚኖር ሕግ ነው። ሕገ ልቦና በሰው ሁሉ ልብ የሚገኝ እያንዳንዱን ሰው ማንም ሳያስተምረው: ክፉውንና ደጉን ለይቶ ሳይነግሩት እንዲያውቅ የሚያደርገው ነው። እውነተኛ ሰው ምንም ባይማር በዚህ በሕገ ልቦና ወይም በሕገ ተፈጥሮ መሰረት እውነትን ከሐሰት: ጽድቅን ከኃጢአት: ደጉን ከክፉ ለይቶ ያውቃል። ከዚህም የተነሣ እውነቱን ይናገራል: ይሰራል ከክፉም ይርቃል።
+። ስለ ሕገ ተፈጥሮ (ሕገ ልቦና) ቅዱሳት መጽሐፍት በተለያየ መንገድ ይመሰክራሉ። ስለዚህም ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ:-
፤ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።
፤ ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤
፤ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና።
፤ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤
፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። (ወደ ሮሜ ሰዎች ምዕ. 2÷11-15)
+ይኸ ሕገ ልቦና የተባለው ያን ጊዜ በተፈጥሮ እንደተሰጠ ያለ የጸናም ሕግ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በሕገ ልቦና ብቻ ሊጠበቅ ባለመቻሉ በግድ የጹሑፍ ሕግ አስፈለገ። ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክ በእጁ ጽፎ ሌላ ሕግን በሙሴ አማካይነት ለጊዜው ለእሥራኤል ወገን ፍጻሜው ግን ለሰው ልጅ ሁሉ ሰጥቷል። ቀጥሎም የጌታ ደቀ መዛሙርት ሐዲሱን የኪዳን ሕግ (ስድስቱን ቃላት ወንጌል) በጹሑፍ አበርክተዋል።
**።።2።። አሠርቱ ቃላት:** አሠርቱ ትዕዛዛት: አሠርቱ ሕግጋት: ሕገ መጽሐፍ(ሕገ ኦሪት):-
የሚባሉት እግዚአብሔር አምላክ ግንኙነቱን ከእስራኤል ህዝብ ጋር በማድረግ መገናኛ ይሆኑ ዘንድ የሠራቸውና የደነገጋቸው ሲሆኑ: በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ አሠርቱ ቃላት እየተባሉ የሚጠሩ ናቸው። እነዚህም

እግዚአብሔር በሁለት ሠሌዳ ጽፎ ለእስራኤል ያስተላለፈው ሕግ ነው።
ሁለቱ የሕግ ጽላት የአስርቱ ቃላት ማደሪያ ሠሌዳ ሁነው የተሰጡ ናቸው። እንደ ሊቃውንቱ አስተያየት በአንደኛው ጽላት ሦስት ቃላት እግዚአብሔር ወይም እግዚአብሔር አምላክን የሚመለከቱ ለእርሱ ልናደርግና ልንፈፅመው የሚገባንን የሚገልጡ ናቸው። በሁለተኛው ጽላት ደግሞ ሰባት አንቀጾች ተጽፈውበታል: ይኸውም ሰውን የሚመለከቱ ማለት ሰው አንዱ ለሌላው ሊያደርገውና ሊፈጽመው የሚገባውን የሚያሳዩ አሠርቱ ቃላት በመጀመሪያ ለሰው መመሪያ እንዲሆኑ በጽሁፍ የተላለፉ ህግጋት ናቸው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በመጀመሪያ በሕገ ልቦና እንዲሁም በሕገ ህሊና በሕግ ሊጸና ለእግዚአብሔርም ሊታዘዝ ተፈጥሮ ነበር: ይህ ግን ባለመቻሉ በጧትና በማታ እያነበበ: እያየም ሰው የሆነ ሁሉ እንዲጠብቀውና እንዲፈጽመው እግዚአብሔር አምላክ ስለፈቃደ ሕጉን በጽሁፍ ሰጠው እነዚህ በጽሁፍ የተላለፉ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለክርስቲያኑ ህዝብ አሁንም አስፈላጊዎች ናቸው።
+ ከአሠርቱ ቃላት ዘጠኙ ተጠብቀው አንደኛው እንኳን ከፈረሠ አሠርቱ ሕግጋት ሁሉ እንደፈረሱ ይገመታል እንጂ የዘጠኙ መጠበቅ ምንም ዋጋ የለውም። ለምሳሌ አሥር በር ያለው ቤት ቢኖር ዘጠኙ በሮች ቢዘጉና አንዱ ክፍቱን ቢያድር: ሌባ ክፍት በሆነው በአንደኛው በር ገብቶ ንብረቱን ሁሉ ከወሰደው የዘጠኙ በሮች መዘጋት ምንም ጥቅም አላስገኝም ማለት ነው የአንደኛው መከፈት ለንብረቱ መጥፋት ምክንያት ሆኗልና። አሠርቱ ቃላትም በትክክል ካልተጠበቁ ዋጋ የማያሰጡ መሆናቸውን ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ሲል ያስረዳል:-
" ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ። አትግደል ብሎአልና፤"
(የያዕቆብ መልእክት 2:10)
።።።።።።።።።
10 ቱ ትዕዛዛት እነማን ናቸው
።።።።።።።።።
>አንቀጽ 1:-
" ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።"
(ኦሪት ዘጸአት 20:3)
።።።
>አንቀጽ 2:-
" የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና። "
(ኦሪት ዘጸአት 20:7)
።።።
>አንቀጽ 3:-
" የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።"
(ኦሪት ዘጸአት 20:8)
።።።
>አንቀጽ 4:-
" አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።"
(ኦሪት ዘጸአት 20:12)
።።።
>አንቀጽ 5:-
፤ አትግደል።
(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:13)
።።።

>አንቀጽ 6:-

፤ አታመንዝር።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:14)

፡፡፡፡፡፡

>አንቀጽ 7:-

፤ አትስረቅ።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:15)

፡፡፡፡፡፡

>አንቀጽ 8:-

፤ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:16)

፡፡፡፡፡፡

>አንቀጽ 9

፤ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።

(ኦሪት ዘጸአት ምዕ. 20:17)

፡፡፡፡፡፡

>አንቀጽ 10

" ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ፤ "

(ኦሪት ዘሌዋውያን 19:18)

++++++

**።።3።። ስድስቱ ሕግጋት (ትዕዛዘተ) ወንጌል:-**

እንደ ብሉይ ኪዳን እምነት ስርዓት ህግን እንደፈፀመ የሚቆጠረው ፍፁምም አይሁዳዊ ነው የሚባለው አሠርቱ ቃላተ ኦሪትን የጠበቀው ነበር። በሐዲስ ኪዳንም አሠርቱ ቃላት ኦሪት ምንም ሳይነኩ እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ ሌሎችም አዲሶች ሕጎች አስፈለጉ። አሠርቱ ቃላተ ኦሪት መጠበቃቸውንና እንዳሉም መጽናታቸውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

፤ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።

፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። (የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:17-18) ሲል ግልጽ አድርጎ ተናግሯል።

+ከዚህ በተጨማሪ ግን እነዚህኑ አሠርቱ ቃላትን በስድስቱ አንቀጽ አጠቃሎና አሳጥሮ ቃላተ ወንጌል ወይም ትዕዛዛተ ወንጌል ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ግን እላችኋለሁ እያለ አጥብቆ: አጽንቶና ወስኖ ተናግሮ ይገኛል።

አሁንም የሐዲስ ኪዳንን ህግጋት ስናቀርብ እነዚህ የብሉይ ኪዳን ህግጋት ለሐዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ሆነው አጥረውና ተጠቃልለው በስድስት ቃላት ይቅረቡ እንጂ አሁንም መሠረቶቹ አሠርቱ ቃላት ናቸው።

ሆኖም አጥረው: ተጠቃለው ከበድም ብለው ለሐዲስ ኪዳን መታወቂያ መለያም ሕግ ሆነው የቀረቡ ሲሆን እነዚህን ሕግጋት ለይቶ: ጠንቅቆ ማወቅና መጠቀም በጣም አስፈላጊ በመሆኑ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:-

፡፡፡፡፡፡

>አንቀጽ 1:-

አትግደል ላለው

" ለቀደሙት። አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።"

+++++++

" እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።"

(የማቴዎስ ወንጌል 5:21÷22)

::::::

>አንቀጽ 2:-

አታመንዝር ላለው

" አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል።"

+++++++

" እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።"

(የማቴዎስ ወንጌል 5:27÷28)

::::::

>አንቀጽ 3:-

መፍታት እንደማይገባ

፤ ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ።

++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:31÷32)

::::::

>አንቀጽ 4:-

ፈጽመህ አትማል ላለው

፤ ደግሞ ለቀደሙት። በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል።

+++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ። ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤

፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤

፤ በራስህም አትማል፥ አንዷቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና።

፤ ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:33-37)

::::::

>አንቀጽ 5:-

"ክፉውን በክፉ አትቃወሙ"

፤ ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።

+++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:38-39)

::::::

>አንቀጽ 6:-

"ጠላትህን ስለመውደድ"

፤ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።

+++++++

፤ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም

መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።
፤ የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?
፤ ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?
፤ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:43-48)
።።4።። አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን:-
ስድስቱ ቃላተ ወንጌል የአስርቱ ቃላት ኦሪት መጠበቂያና ማጠረያ እንደሆኑ አንድም አሠርቱ ቃላት በስድስት ቃላተ ወንጌል እንደጸኑ ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ደግሞ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን ይታጠራሉ: ይጸናሉ: ፍጹምነታቸው እንዲታወቅ ይሆናል።
እነዚህ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን የሕግ ፈጻሚነት ምልክትና የፍፁምነት መታወቂያ ትሩፋት ናቸው እንጂ ሕግጋት አይደሉም። እነዚህ የፍጹምነት: የብፅዕና የቅድስና መታወቂያ አንቀጾች ጌታ የተናገራቸው ሰሆኑ የፍፁምነት ማዕረግ የሚሰጡ ናቸው።
እነዚህ አሥሩ አንቀጸ ብፁዓን ወይም ሕገ ትሩፋት የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:-
1. " በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:3)
2. " የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:4)
3. " የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:5)
4. " ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:6)
5. " የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:7)
6. " ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:8)
7. " የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:9)
8. " ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።"
(የማቴዎስ ወንጌል 5:10)
9. ፤ ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ።
፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 5:11-12)
10. " ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 13:17)
+ሙሴ ዘጠኙን ሕግጋት በኦሪት ዘፀአት 20:17 ተናግሮ አሥረኛውን በኦሪት ዘሌዋውያን 19:18 እንዳመጣው ጌታም የተናገረውን አስሩን አንቀጸ ብፁዓን 9 ኙን በማቴዎስ ወንጌል ተናግሮ አስረኛውን በዮሐንስ ወንጌል ያመጣዋል። ይህም የመጨረሻው የብፅዕና አንቀጽ ትህትና ነው።
።።5።። በለተ ምጽአት ከጌታችን የምንጠየቃቸውና የምንመልሳቸው 6 ጥያቄዎች:-
ትንሣኤ ዘጉባኤ:- ትንሳኤ ዘጉባኤ ማለት በዕለተ ምጽአት ጌታ ለፍርድ ሲመጣ በእርሱ ትእዛዝ (በአዋጅ ድምፅ)

ተለያይተው በተለያየ ስፍራ ይኖሩ የነበሩ ነፍስና ሥጋ ከሞት በኋላ በነፍስና ስጋ ህይወት መገኘትና ተዋህዶ መነሳት ማለት ነው። ይህ ሰውን ብቻ የሚመለከት ነው።
+++++++
" በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኵሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጕስቍልና። "
(ትንቢተ ዳንኤል 12:2)
" በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።"
(የዮሐንስ ወንጌል 5:28-29)
" እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።"
(የዮሐንስ ራእይ 22:12)
" እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።"
(የዮሐንስ ራእይ 1:7)
፤ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤
፤ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።
፤ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።
(1 ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ምዕ. 4:16-18)
። ። ። ። ። ። ። ።
*1 የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው ያለቀውና የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል። (ያዕቆብ ዘስሩግ ቁ.91)
*2 ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋህደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ ሬሳ ይሆናሉ አጥንቶችና ጂማቶች ከስጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ። እስኪነሱ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናል።
*3 ሶስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቅዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጓድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈል ወንድ በአቅመ አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ: ሴት በአቅመ ሔዋን የአስራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው በአርባ ቀን በእናቱ ማኅፀን ደም ሆኖ የወረደ ጽንስ ሳይቀር እያንዳንዱ የሥራውን ዋጋ ሊቀበል ይነሳሉ።
++++++
፤ የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤
፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥
፤ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።
፤ ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።
፤ ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥
፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።
፤ ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?
፤ እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?

፤ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?
፤ ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።
፤ በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።
፤ ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥
፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።
፤ እነርሱ ደግሞ ይመልሱና። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል።
፤ ያን ጊዜ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።
፤ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።
(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 25:31-46)

።።። ተፈጸመ ።።።
ጌታችን መድኃኒታችና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰራቸው ሕግጋት እንድንፈጽም ይርዳን: አለማመናችንን ይርዳው አሜን።
ወ ስ ብ ሐ ት ለ እ ግ ዚ አ ብ ሔ ር
ወ ለ ወ ላ ዲ ቱ ድ ን ግ ል
ወ ለ መ ስ ቀ ሉ ክ ቡ ር

የኖኅ ቀስተ ደመና

---

በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ
>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>......
እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኖኅ ከእግዚአብሔር ዘንድ የጥፋት ውሃ ዳግመኛ እንዳይመጣ ምልክት አድርጎ በተቀበላት አስደናቂ የቀለማት ሕብር ባላት ቀስተ ደመና ትመሰላለች (ዘፍ ፱÷፷-፲፯)፤ ይኸውም ኖኅ ከመርከብ ከወጣ በኋላ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ያን ጊዜ ዳግመኛ “ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልዕዋ ለምድር” (ብዙ ተባዙ ምድርን ምሏት) ቢለው፤ ኖህም በሐዘን ኾኖ “እኔ ብበዛ ምን ያደርግልኛል፤ የኔ ልጆች ኀጢአት ከመሥራት አያቋርጡ፤ አንተም በእውነት ፈርደኽ ልታጠፋቸው አለ፤ ጌታም ቸር ነውና ዳግመኛ በንፍር ውሃ እንዳላጠፋት ‹‹ቀስትየ እሠይም በደመና ወትከውን ተአምረ ለኪዳንየ ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ወማእከለ ምድር›› (በናንተና በኔ መኻከል በምድርም መኻከል ለመሐላዬ ምልክት አድርጌ ቀስቴን በደመና አኖራለኊ) “ወይከውን ሶበ አጼምን ደመና ላዕለ ምድር ታስተርኢ ቀስትየ ላዕለ ደመና” (ደመናን በምድር በጋረድኊ ጊዜ እንዲኽ ይኾናል፤ ቀስቴ በደመናው ላይ ይታያል) ‹‹ወትወጽእ ቀስትየ ውስተ ደመና ወእሬእያ ከመ እዘከር ኪዳንየ ዘለዓለም በማእከሌየ ወማእከለ ኵሉ ዘሥጋ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ዘሀሎ መልዕልተ ምድር›› (ቀስተ ኪዳኔ ከደመና ውስጥ ትወጣለች፤ በምድርም ላይ ባለ ሕይወት ባለው በሥጋዊ ፍጥረት ኹሉ መኻከልና በኔ መኻከል ያለ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ኪዳኔንም ዐስብ ዘንድ እሷን አመለከታለኊ) ዘፍ ፱÷፲፪-፲፯ በማለት አስደናቂ ሕብር ያላት ቀስተ ደመና በዐርበኛ (በቀስተኛ) ልማድ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕብረ ቀለማት አስውቦ አሳይቶታል።

ጌታ ይኽነን ሕብር ለኖኅ ማሳየቱ፤ እንግዲኽ ወዲኽ ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰውን በንፍር ውሃ አላጠፋውም ሲለው ሲኾን ፍጻሜው ግን ደመና የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነውና ከእናቴ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቼ ተወልጄ ሰውን አድነዋለኊ ሲል ነው። ይኽነንም በርካቶች ሊቃውንት በሰፊው ተርጒመውታል፤ ከነዚኽ መኻከል ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም፣ አባ ጊዮርጊስና አባ ጽጌ ድንግል ይገኙበታል፤ ይኸውም በእጅጉ ደስ የሚያሰኘው ጌታ ለወዳጁ ለኖኅ በሰጠው ቀስተ ደመና ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውሃ እንዳላጠፋት ኹሉ ለእውነተኛዋ ምልክት

ለእናቱ ለድንግል ማርያም በሰጣት ቃል ኪዳን ፍጥረቱን አያጠፋምና (ኢሳ ፩÷፱፤ መዝ ፹፰÷፫፤፻፴፩÷፲፫-፲፯)::

ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በአድናቆት ኾኖ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ
‹‹ትእምርተ ኪዳን አንቲ ዘተሰመይኪ ቀስተ ደመናት
ከመ ኢይምጻእ ውስተ ምድር ዳግመ ዝናመ መዓት ››
(ዳግመኛ የመዓት ዝናም ወደ ምድር እንዳይመጣ ቀስተ ደመናት የተባልሽ የኪዳን ምልክት አንቺ ነሽ) በማለት
ከአምላክ የተሰጠችን የድኅነት ምልክት መኾኗን አስተምሯል።
ሊቁ አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያምም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ፡-
‹‹ቀስተ ደመና ማርያም ትእምርተ ኪዳኑ ለኖኅ
ዘእግዚአብሔር ሤመኪ ለተዝካረ ምሕረት ወፍትሕ
ህየንተ ቀሠፋ ለምድር ወአማሰና በአይኅ
በእንቲአኪ አሰርገዋ በጽጌ ኵሉ አቅማሕ
ከመ በከዋክብት አሰርገዎ ለሰማይ ስፋሕ››
(ለምሕረትና ለፍርድ መታሰቢያ አድርጎ ያኖረሽ፤ የኖኅ የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ማርያም፤ ምድርን በንፍር ውኃ ስለመታትና ስለአጠፋት ፈንታ፤ ሰፊ ሰማይን ስፍር ቍጥር በሌላቸው ከዋክብት እንደ አስጌጠው ኹሉ፤ በአንቺ ምክንያት ልዩ ልዩ በኾኑ አበባዎች ፍሬዎች ምድርን አስጌጣት) በማለት አማናዊት ቀስተ ደመና የመባረክ የድኅነት ምልክት የኾነችው ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን መስክረውላታል።

በተለይ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የርስት ሀገሯ የኢትዮጵያ ምእመናን ይኽቺን ቀስተ ደመና ከፍጹም ፍቅራቸው የተነሣ “የማርያም መቀነት” ይሏታል። ምንም ኀጢአታችን ቢበዛም ደጓ እናታችን ግን በኀልጎታ ከልጇ በተሰጣት ቃል ኪዳን ታማልደናለች፤ እናታዊ በረከቷም ኹሌ አይለየነምና እንወዳታለን። አማናዊት ቀስተ ደመናችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ አብዝተሽ ትባርኪን ዘንድ፤ ከልጅሽም ይቅርታን ትለምኝልን ዘንድ እንማፀንሻለን።
ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

ምዕራፍ ሦስት

## 3. ሥርዐተ ተክሊል

ተክሊል የሚባለው ስያሜ የግእዝ ቃል ሲኾን ተቀራራቢ ትርጉም ካላቸው ሁለት ግሶች የወጣ ዘር ወይም ስም ነው። ተክሊል ማለት ከለለ፣ ጋረደ ፣ ብሎ የመጋረድ ፣ የማክበር ጸሎት ለማለት ጸሎተ ተክሊል ተብሏል። ማለትም ሙሽራውና ሙሽራይቱ እንደ መኀናጸፊያ ዘውድ የአርቦን ክብር ተሰጥቷቸው ጸሎት ይደረስላቸዋልና። "ተክሊል" ተቀዳጀ ዘውድ (አክሊል) ደፋ የአርቦን ክብር ተቀበለ ለማለት በሙሽራውና በሙሽራይቱ ራስ ላይ የሚደፋውን የአርቦን አክሊል በመመልከት የወጣ ስም ነው።

ጸሎተ ተክሊል (ምስጢረ ተክሊል) ማለት አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር አንዲት ሴትም ከአንድ ወንድ ጋር ተስማምተው በነጻ ምርጫቸውና ፈቃዳቸው በሚያደርጉት ጋብቻ ላይ ካህኑ ስምምነታቸውን በማጽናት ሁለቱን በእግዚአብሔር ቃል አንድ አካል ለማድረግ የሚጸለየው የጸሎት ሥርዐትና የአንድነት ጸጋን የሚያገኙበት ሚስጢር ነው። ሁለቱን ተጋቢዎች አንድ የሚያደርጋቸው የጌታ ሥጋውና ደሙ ነውና። ስለዚህ የሥርዓተ ተክሊል ፍጻሜ ጸሎተ ቅዳሴ ነው። በመሆኑም ሙሽሮች ሥጋውን ደሙን ይቀበሉ ዘንድ ይገባል።

### 3.1 ጋብቻ

ሁለቱን አንድ ለማድረግ የሚጸለየው የጸሎት አይነትና ጠቅላላ ሥርዐት ምስጢረ ተክሊል (ሥርዐተ ተክሊል) ሲባል የሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች አንድ ለአንድ መወሰን ወይም የአንድ ወንድና የአንዲት ሴት የጋራ አንድነት ጋብቻ ይባላል።

### 3.1.1 የጋብቻ አመሠራረት

ጋብቻን የመሠረተው እግዚአብሔር ነው። "እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር ....ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው ብዙ ተባዙም ምድርንም ሙላት" /ዘፍ 1:27-28/አላቸው። ከዚህም "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ይጣበቃል ፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናል" /ዘፍ 2:22-24/። ይህ አምላካዊ ምስክርነት ጋብቻ ሊታበል የማይችል እውነተኛ ፣ የማይናወጥ ጽኑና ሁለት የተቃራኒ ጾታዎች ብቻ የተሰጠ ልዩ ጸጋ መኾኑን በግልጽ ያሳየናል። ይህንኑ ጋብቻ በሐዲስ ኪዳን አጽድቆት እናገኛለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሐዲስ ኪዳን አጽንቶ በትምህርቱም በሰርግ ቤትም በመገኘት ጋብቻን ባረከ ምስጢርነቱንም አጸደቀ /ዮሐ 2:1-11/። ፈሪሳውያን ስለ ባልና ሚስት መፋታት ወይም አለመፋታት አስመልክቶ በጠየቁት ጊዜ የሰጠው መልስ ነገሩን በማጽናት ባልና ሚስት አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም ፣ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይችልም አይገባውም ሲል ተናግሯል /ማቴ 19:3-9/። ቅዱስ ጳውሎስም የጋብቻን ክብር ትርጉሙን ምሳሌውን በመግለጽ ሙሽራውን በክርስቶስ ፣ ሙሽራይቱን በቤተክርስቲያን እየመሰለ ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን እንደማይለይ ባልም ከሚስቱ ሊለይ እንደማይገባ ሰፋ ያለ መብራሪያ ሰጥቶ አስተምሯል፣ ጽፏልም

ምስጢረ ተክሊል በዚህ መልክ የተመሠረተ ከፍተኛ ዓላማ ያለው ቅዱስ እግዚአብሔር ያዘዘው በመሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ የተደገፈ የሰው ዘር የሆነ ሁሉ ሊያደርገው ፣ ሊፈጽመው የሚገባ ነው።

### 3.1.2 የጋብቻ ዓላማ

ጋብቻ ሦስት ዓላማዎች አሉት። እነርሱም ፦

1. ዘር ለመተካት ፦

እግዚአብሔር አምላክ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት" ባለው አምላካዊ ቃሉ ዘር መተካት እንደሚገባ የሚያስነዝብ ነው /ዘፍ.1:28/። በዚህም አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ፤ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ ጸንተው በሕጋዊ ጋብቻቸው ዘር ለመተው ፣ ምትክ ለማድረግ እንዲችሉ ነው።

2. መረዳዳት ፦

በመልኩና በምሳሌው አክብሮ የፈጠረው የሰው ልጅ ሕይወት አድካሚና አስቸጋሪ እንዳይሆን በመደጋገፍና በመረዳዳት በፍቅርና በደስታ መልካም የሆነ ሕይወት እንዲኖር "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም እረዳት እንፍጠርለት" አለ
/ዘፍ 1:26/። የሰውን ድክመት የሚያውቅ ነውና።

3. ከዝሙት መጠበቅ ፦

የሰው ልጅ በኃጢአት ምክንያት ከአምላኩ ያገኘውን ክብር ቅድስና እንዳያጣ ከሚያረክስ ከዝሙት እንዲጠበቅ "አታመንዝር" በማለት አስተማረው። ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን የደረሱም በሥጋዊ ፍትወት ተነሣሥተው በዝሙት እዳይወርቁና ሰውነታቸውን እንዳያረክሱ በቅዱስ ጋብቻ መወሰን ይኖርባቸዋል። ቅዱስ ጳውሎስ "ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ፣ ለእያንዳንዲቱም ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት" በማለት ያስተማረው ለዚህ ነው /1 ኛ ቆሮ 7:2/።

- በጋብቻ ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ

ጥያቄ ፦ በጋብቻ መፋታት ይቻላል ፤ ድጋሜ ጋብቻስ የሚፈቀደው እንደት ነው?

መልስ ፦ ባልና ሚስት አንድ አካል እንጂ ሁለት አይደሉም ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሊለይ የሚችል

የለም ሲል ክርስቶስ እንደተናገረው
ሁለቱ ወገኖች ተስማምተው ከተጋቡ በኃላ በምንም መልክ መለያየት ፣ መፋታት አይገባቸውም።

እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይገባውም እንደተባለ ባልና ሚስት በሥጋ ወደሙ አንድ ከሆኑ በኃላ የተገባቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰው ሊለያዩ ወይም ሊፋቱ አይገባቸውም። ጋብቻ የማይፈታ ሚስጢር ነው። ባልና ሚስት አንድ አካል እንጂ ሁለት አይደሉም ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሊለይ የሚችል የለም። ባልና ሚስት ሊለያዩ የሚችሉት ምክንያቶች ከሁለት አንዱ በዝሙት የተያዘ እንደሆነ። እንዲሁም በመካከላቸው የሃይማኖት ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ ነው። ከዚህ ውጭ ግን ሰነፊች፣ መከነች ፣ ጠቆረች ፣ ደኸየች በሚሉት ተልካሻ ምክንያቶች መፋታት አጥብቆ የተከለከለ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በሚስትህ ታስረህ እንደሆነ መፋታት አትሻ" ብሏል /1 ኛ ቆሮ 7:27/። እንዲሁም መለያየት ፣ መፋታት እንደማይገባ ሲያስገነዝብ "ሴት ከባልዋ አትለይ፣ ወንድም ከሚስቱ አይለይ። ሁላችሁም በጌታ ትእዛዝ አንድ ሆናችሁ ኑሩ" ብሏል /1 ኛ ቆሮ 11:11/።

ድጋሚ ጋብቻ ይፈቀዳልን? ለሚለው ጥያቄም ስንመለከት ለፍቺ የሚያደርሱ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው? የሚለው መታየት ይኖርበታል። ለፍቺ ምክንያቶች ከላይ እንደተገለጸው የሃይማኖት ልዩነትና ከሌላ አካል ጋር በዝሙት መውደቅ ናቸው። ከባልና ሚስት አንዱ ሃይማኖቱን ቢለውጥ ፣ ያልለወጠው ወገን በቤተክርስቲያን አባቶች ያስመክራል። ነገር ግን ለዋጩ ክፍል በፍጹም አልመለስም ካለ ፍቺው በቤተክርስቲያን አባቶች ይጸናል። ሃይማኖቱን ያልጠበቀው እንደሞተ ተቆጥሮ ለብቻዬ መኖር ያቅተኛል ካለ ንጽህናዋን የጠበቀችውን በሕገ ቤተክርስቲያን ያገባል። በሌላ በኩል ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈቀደው በዝሙት ምክንያት ሚስቱን ወይም ባልዋን ለፈታች ወይም ለፈታ ነው።

ቃል ኪዳኑን የጠበቀው ክፍል ለቤተክርስቲያን ነግሮ ለብቻው መኖር የሚያቅተው ከሆነ ንጽህናዋን የጠበቀችውን በዝሙት ምክንያት ያልተፈታችውን ያገባ ዘንድ ወይም ታገባ ዘንድ ይፈቀድለታል ፤ ይፈቀድላታል። በተጨማሪም ከሁለት አንዱ በሞት ቢለይ በሕይወት የቀረው ቀሪውን ጊዜ በብቸኝነት ማሳለፍ ይከብደኛል ካለ በቤተክርስቲያን ሥርዐት ተወስኖ ያገባ ዘንድ ይፈቀድለታል /1 ኛ ቆሮ 7:39/። ሁለተኛ ጋብቻ በሥጋ ወደሙ ይከናወናል እንጂ ሥርዐተ ተክሊል አይደረግም።

ጥያቄ ፦ ሰው ካገባ በኃላ ዐርባ ቀን አይጾምም የሚሉ አሉ። አንዳዶች ደግሞ ተጋቢዎቹ እስከ አርባ ቀን ድረስ መኝታ መለየት አለባቸው ይላሉ። በዚህ ላይ የቤተክርስቲያናችንን አስተምህሮ ምንድን ነው?

መልስ ፦ በፍትሐ ነገስት የአንድምታ ትርጓሜ ላይ ያለ ጸሎትና ሥጋ ወደሙ ተጋቢዎች መጋባት እንደሌለባቸው ያስረዳል። በቤተክርስቲያን የሚካሔደውን የጋብቻ ሥርዐት ሲያብራራ ፦ "የወንድ ወገን ሙሽራን ይዘው በሰሜን በኩል የሴት ወገኖች ሙሽራዋን ይዘው በደቡብ ቀኩል ይገባሉ። በደቡብ በኩል ምንጣፍ ተነጥፎ ወንበር ተዘጋጅቶ ጸሎተ ተክሊል ይፈጽማሉ። ሙሽሮች በዚሁ ዕለት አስቀድሰውና ቆርበው ከወጡ በኃላ ባሉት ዐርባ ቀናት ሙሽራውም ከአባቱ ጋር እየተኛ ሙሽራይቱም ከእናቷ ጋር እየተኛች በመካከሉ እያስቀደሱ እየቆረቡ ለ 40 ቀን ይቆዩ። ለ 40 ቀን ከቆዩ በኃላ ሠርግ ያድርጉላቸው " ይላል።

አርባ ቀን የተባለው በጸሎተ ተክሊልና ሠርጉ በሚደረግበት ቀን መካከል ያሉትና ቀናት ነው። ከዚህ የምንረዳው ሰርግ ማለት ተክሊሊ አለመሆኑና እነዚህ የተለያዩበትን ጠንቅቆ መረዳት ይገባናል። አሁን ጊዜ ልማድ ተክሊልና ሰርግ በብዛት የሚፈጸሙት በአንድ ቀን ነው። በዚህ ጊዜ ከሚስጢረ ቁርባን በኃላ ቢያንስ ሁለት ቀናት መጠበቅ ይገባል የሚለው የቤተክርስቲያናችን ሥርዐት ነው። ስለዚህም አርባ ቀን ሲልም በተክሊልና በሠርጉ መካከል ያለው ጊዜ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ሌላው ሊስተዋል የሚገባው ነጥብ አሁን ያለው የሰርግ ሥርዐት ስሕተት ነው ለማለት አይደለም።

ጥያቄ ፦ እንደ ቤተክርስቲያናችን ሥርዐት ሁለቱ ተጋቢዎች ጋብቻቸውን አጽንተው በአንድነት ሲኖሩ የሰማኒያ ጋብቻ ይባላል። ለምን የሰማኒያ ጋብቻ ተባለ?

መልስ ፦ የሰማኒያ ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው። ለአዳም አጋሩን በኑሮ ዘመኑ የምታግዘውን ሔዋን ወደ ገነት የገባችው በተፈጠረች በ 80 ቀኗ ነው። "ሚስቱንም በሰማንያ ቀን አስገባት" እንዲል /መጽሐፈ ኩፋሌ 4:9/። ሔዋን ወደ ገነት ገብታ ከአዳም ጋር በአንድነት ፣ በደስታ አንድ የሆነችው በሰማኒኛው ቀኗ ነው። እንደዚሁም ሁሉ ጋብቻ ሁለት ተጋቢዎች ወደ ጋብቻ ሕይወት (የአንድነት ሕይወት) የሚገቡበት ሥርዐት ነውና የሰማኒያ ጋብቻ የሚለው ስያሜ ሊሰጠው ተችሏል።

ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "የዘመኖቻችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት ፤ ቢበረታም ሰማኒያ ዓመት ነው" የተናገረውን ነው /መዝ 90:10/። "ሰማኒያ ዓመት" የሚለው አገላለጽ የዕድሜ ፍጻሜን ፣ ጣሪያ ገደብን የሚያስረዳ እንደሆነ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይናገራሉ። ይህም ጋብቻ ፍጹም አንድነት ያለው፣ እስከ ዕድሜ ልክ አብረው የሚኳዙት ሕይወት መሆኑን ይገልጻል። ተጋቢዎቹም በቤተክርስቲያንና በሕዝብ ፊት የገቡት ቃል ኪዳንም የሚያስረዳው ይህንኑ ነው። ሙሽራው የሙሽራይቱን ቀኝ ይዞ በካህኑ እየተመራ "እኔ እገሌ የሕግ ሚስት ትሆነኝ ዘንድ እገሊትን ወድጄ ተቀብያታለሁ ፣ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ በሥራዋ ሁሉ በተቻለኝ እረዳታለሁ፣ በህመሟና በጤናዋና በሐዘኗም ጊዜ ከእርሷ ጋር እሆናለሁ። መከነች ሰነፈች በማለት ይህንንም በመሳሰለው ምክንያት ሁሉ በልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝ ከእርሷ በሞት እስክለይ ድረስ አልተዋትም። ወድጄ ተቀብያታለሁና ስለዚህም በእግዚአብሔርና በተቀደሰችው በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጉባኤ ፊት በመሐላ ቃሌን እሰጣለሁ " ይላል። ሙሽራይቱም የሙሽራውን እጅ በቀኝ እጇ ይዛ በካህኑ እየተመራች ልክ ሙሽራው የፈጸመውን ዓይነት ቃል ኪዳን ትፈጽማለች። ስለዚህ ጋብቻ በመንፈሳዊ ሆነ በዓለማዊ ጋብቻቸውን ለፈጸሙ ሰዎች የሰማኒያ ጋብቻ በሚል ስያሜ ሲጠሩ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

የሃዋርያት ስራ> ክፍል ፩< በእንተ ዕርገት፤
=====================================.

ወዘንተ ይብሎሙ ተለዐለ ወነሰኣቶ ደመና ወዓረገ ሰማየ እንዘ እምንቱ ይነስጽሩ ኃቤሁ ወተሰወረ እማኣዕንቲሆሙ።
[ይህንንም እየነገራቸው ኮፍኮፍ ኣለ ደመናም ተቀበለው እነሱ እያዩትም ወደ ሰማይ ዐረገ ከዓይናቸው ተሰወረ።]

ወኣስተርኣርዎሙ ክለኤቱ እደው ወቆሙ ኃቤሆሙ ውይለብሱ ጸዕዳ
ወይቤልዎሙ ኣንትሙ ሰብእ ገሊላ ምንትኑ ቆምክሙ ትራዩ ሰማይ ዝውእቱ ኢየሱስ ዘዐረገ እምሃቤክሙ ውስተ ሰማይ ወወከማሁ ካዕበ ይመጽእ በከመ ርኢክምዎ ይዓርግ ሰማየ።
[ ሁለት ሰዎች ነጫጭ ልብስ ለብሰው ባጠገባቸው ቁመው ታዩኣቸው ፣
እናንተ የገሊላ ሰዎች ለምን ወደ ላይ እያያችሁ ቁማቹኃል ከእናንተ ወደ ሰማይ ያረገው ይህ ኢየሱስ ነው ፧እንዲሁም ወደ ሰማይ ሲያርግ አንዳያችሁት ዳግመኛ ይመጣል ኣላቸው።]

---------------------------------------------------------------------------

ኣሜን ወስብሓት ለእግዚኣብሄር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር